# ለዘላቂ የኢትዮጵያ ህልውና፣ ሰላምና እድገት ዋስትና የሚሰጥ በአል

## ክፍል አንድ

ለሚ ዋቄ 12-17-14

ሃያኛውን ዓመት የኢፌዴሪ ሕገመንግስት የፀደቀበትንና ዘጠነኛውን የኢተዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀን ካከበርን ሳምንት አስቆጥረናል። በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መዲና አሶሳ የተከበረውን ዘጠነኛውን የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ቀን አስመልክቶ የተለያዩ ወገኖቸ አስተያየት ሰንዝረዋል። በበአሉ ዙሪያ የተሰነዘሩት አስተያየቶች አብዛኞቹ "እርስ በርስ የሚያስተዋውቅና በመከባበር ላይ ለተመሰረተ ጠንካራ አንድነት መሰረት የሚጥል ነው" የሚል ቃና ያላቸው ናቸው። የተለያየ ብሄሮች፣ በሄረሰቦችና ህዝቦች አባላት የሆኑ ኢትዮጵያውያን እለቱን "የራሴ በአል ነው" በሚል መንፈስ አክብረውታል፤ አስበውታል።

ዘንድሮ የተከበረው 9ኛው የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በአል ከመደረሱ ሁለትና ሶስት ቀናት ቀደም በሎ ጀምሮ ከአፀደ ሕፃናት እስከ ሁለተኛ ደረጃ የሚማሩ ሕፃናትና ወጣት ተማሪዎች የየብሄራቸውን እነዲሁም የማንኛውንም ደስ ያላቸውን ብሄር አልባሳት ለብሰው አዲስ አበባን ጨምሮ ለተለያዩ የሃገራችን ከተሞች ድምቀት ሰጥተው አለቱን ማክበራቸው በአሉ ምን ያህል በመላው ኢትዮጰያውያን ትኩረት ተሰጥቶት እንደተከበረና ለወደፊትም እንደሚከበር ያረጋግጣል። በየትምህርት ቤቱ በአሉን ያከበሩት ህፃናትና ወጣቶች በየቤቱ ያለውን የኢትዮጵያ ህዝብ ስሜት እንደሚያንፀባርቅ ልብ በሉ።

የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች በዓል እነዲከበር መደረጉን በግልፅ ደፍሮ የተቃወመ ወገን ባይሰማም፣ የበአሉን ዋጋ ለማሳነስና ለማጣጣል የሚከሩ ግን አልታጡም። የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦቸና ሕዝቦች ራስን በራስ የማስተዳደር - በቋንቋ የመስራት፣ በቋንቋ የመማር፣ ባህልን የማሳደግና የመግለፅ፣ ታሪክን የመንከባከብ . . . በህገመንግስት መረጋገጡ የጎመዘዛቸውና እንቅልፍ የነሳቸው ጥቂት የባለፉ ስርአት ውርጄዎች ናቸው የበአሉን ዋጋ ሊያሳንሱና ሊያንቋሽሹ የሞከሩት።

እነዚህ ጥቂት ያለፉ ስርአት ውርዴዎች አፋቸውን ሞልተው በአሉን መቃወም፤ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች በፍቃዳቸው በመሰረቷት አዲሲቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ውጉዝ መሆኑን ስለሚያውቁ የመብት ተቆረቋሪ በመመስል "ጭፈራ ለብሄሮችና ብሄረሰቦቸ ምን ይፈይዳል" በሚል ቃና ነበር የተናገሩተ፤ "የአዛኝ ቅቤ አንጓች" እንዲሉ ። በፖለቲከኝነትና በጋዜጠኝነት ሽፋን የሻአቢያ ተላላኪዎችን ዓላማ የሚያስፈፅሙ ቅጥረኞች ከሁለት ዓመት በፊት በአሉን "የብሄሮች ብሄረሰቦቸ ምብት እስከመጨፈር" የሚል የተሰነዘረን ቧልት ውስጥ ውስጡን ሲያነሾካሹኩ ሰምተናል።

ህገመንግስታዊ ስርአቱ ባረጋገጠው ሃሳብን የመግለፅ ነፃነት ተጠቅመው የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀን መከበርና የብሄሮቹ፣ ብሄረሰቦቹና ሕዝቦቹ ማንነት ጎለቶ መታየት "ለሃገሪቱ አንድነት አደጋ አለው" የሚል ያረጀ ሞሾ ያወረዱም አልጣጡም፤ በጋዜጦች ላይ በወጡ ፅሁፎች። ይህ "የብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች መብት መከበር አንድነት ያናጋል" የሚል ሙሾ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ በሄረሰቦችና ሕዝቦች በየአቅጣጫው በከፈቱት የበሄራዊ ነፃነት የትጥቅ ትግል ተፋፍሞ ከነበረበት ግዜ አንስቶ በአሃዳዊ ስርአት ገዢዎችና ቀላጤዎች እነደፀሎት ሲደገመ የኖረ የሰለቸ ወሬ ነው። ከደርግ ስርአት መውደቅ በኋላም ይህንኑ አሮጌ ለቅሶ ማላዘንን ስራዬ ብለው የተያያዙ አሉ።

ለዚህ አስረጂነት አዲሰ አድማስ የተባለው ሳምንታዊ የአማርጫ ጋዜጣ በታህሳስ 4፣ 2007 ዕትሙ በነፃ አስተያየተ አምዱ ላይ "የ 'ብሄር ብሄረሰቦች በአል' ፋይዳው ምንድነው?" በሚል ርዕስ የቀረበ አንድ ፅሁፍ መመልከት ይቻላል። ባዩልኝ አያሌው በተባሉ ፀሀፊ የቀረበው ይህ ፅሁፍ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና የህዝቦችን ቀን መከበርን እንደ አደጋ ነው የተመለከተው።

*የባዩልኝ አያሌው ፅሁፍ " ሰኞ ጠዋተ ከቤቴ ስወጣ ያልተለመዱ ነገሮችን አየሁ፡፡ በርካታ ህጻናት የተለያዩ ብሔረሰቦችን ልብስ ለብሰውና በወላጆቻቸው እጃቸውን ተይዘው በመንገድ ላይ አለፉኝ፡፡ የዘንድሮው 'በዓል' ከበድ እንዳለ ቀልቤ እየነገረኝ ነው፡፡ ከየትና እንዴት እንደተከሰተ ያላወቅሁት ጥያቄ አእምሮዬን ሰቅዞ ያዘኝ፡፡ እንዲህ የሚል 'እነዚህ ህጻናት*

*የየትኛውን ብሔረሰብ ልብስ ነው የለበሱት?’ ወይንም ‘ወላጆቻቸው ህጻናቱን የየትኛውን ብሔረሰብ ልብስ ነው ያለበሷቸው?’ አእምሮዬ ምላሽ ፍለጋ ቃተተ፡፡*

*ይህንን እያሰላሰልኩ ሳዘግም አንድ በጥቂቱ የምንግባባ ወዳጄን ከፊት ለፊቴ ሲመጣ አየሁት፡፡ ህጻን ልጁን በእጁ ይዞ በፍጥነት እየተራመደ ነው፡፡ ህጻኑ ላይ አይኔ አረፈ፡፡ የአንድ ብሔረሰብን (የእከሌ ማለቱን አልፈለግሁም፡፡) የባህል ልብስ ለብሶአል፡፡ አባትና ልጅ አጠገቤ ደረሱ፡፡ ወዳጄን ሞቅ አድርጌ ሰላም ካልኩት በኋላ በእርጋታ አንድ ጥያቄ ሰነዘርኩ፡፡*

*‘ልጅህን ወዴት እየወሰድከው ነው?’ ‘ወደ ትምህርት ቤት’አለኝ ፈጥኖ፡፡ ቀጠለናም ‘ዛሬ የብሔረሰቦች ቀንን ያከብራሉ’ አለኝ፡፡ ብዙም ሳያደክመኝ ለጥያቄዬ ስለተመቻቸልኝ እየተደሰትኩ የምፈልገውን ቀለል አድርጌ ጠየቅሁት፡፡ ‘ታዲያ የማንን ብሔረሰብ ልብስ አለበስከው?’ ከብርሃን ፈጥኖ በኩራት መለሰልኝ፡፡ ‘እንዴ ምን ማለትህ ነው፤ የራሴን ነዋ፡፡’ ለጥያቄዬ መልስ ለማግኘት የደከምኩትን ያህል መልሱን ስሰማ አልተደሰትኩም፡፡”* ይላል።

ፀሃፊ ባዩልኝ አያሌው በፅሁፋቸው የገለፁት የተለያዩ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች የማንነት መለያዎችና መገለጫዎች አደባባይ መውጣት፣ ለጆቻቸው ባህላቸውን መውረሳቸው እንዳላስደሰታቸው ነው የገለፁት። ሰዎች ብሄራዊ ማንነታቸውን መግለፃቸው አደጋ አለው ባይ ናቸው።

*ይህን አደጋ ያሉትነ ሲገልፁም “ልብ በሉ! በበዓሉ ቀን ሰዎች የ’የብሔረሰባቸውን’ ልብስ ለብሰው ከቤታቸው ይወጣሉ፡፡ በበዓሉ መከበሪያ ቦታ ላይም የ ‘የራሳቸውን’ ብሔረሰብ ጭፈራ ይጨፍራሉ፡፡ አጋጣሚውንም ካገኙ ስለ ብሔረሰባቸው ታላቅነት ይናገራሉ፡፡ የዚህ ትርፉና ውጤቱ ምንድነው? አንድነት፣ አብሮነት፣ መከባበር… ወይስ ውድድር፣ መቧደንና እኛ እንዲህ ነን ማለት!”* ብለዋል።

እንግዲህ የኢትዮጵያ በሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ቀን መከበርን “የብሄሮች ብሄረሰቦቸ መብት እስከመጨፈር” በሚል ለማንኳጠጥ የሞከሩትም ይሁኑ እንደ አዲስ አድማሱ ፀሃፊ ባዩልኝ አያሌው “የአንድነት መናጋት አደጋ” ሆኖ የታያቸው ዜጎች አመለካከታቸው ሞቶ

የተቀበረው የቀደሞ አሃዳዊ ስርአቶች ቀሪት ነው። በመሆኑም ተፅእኖ መፍጠር የሚያስችል ጉልበት የለውቅም። ይሁን እንጂ ጥቂቶችንም ቢሆን ውዥንብር ውስጥ ሊከቱ ሰለሚችሉ በዝምታ መታለፍ የለባቸውም የሚል ስሜት አሳድሮብኛል። እናም በዚህ ፅሁፍ ከአጠቃላይ  የኢትዮጳያ በሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዘቦች በአል አከባበር መንፈስና በተለይ የዘንድሮውን በአል ካዘጋጀው የቤኒሻንጉል ጉምዝ ሕዝብ ነባራዊ ሁኔታ ጋር አያይዤ ልመለከተው ወድጃለሁ።

ቀደመ ሲል እነደገለፅኩት የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዘቦች ቀን መከበሩ ያልተመቻቸውና በቧልት ዋጋውን ማሳነስ የሚፈለጉ ሰዎች በአመዛኙ የብሄሮችና ብሄረሰቦቸ መብትና ነፃነት መከበሩ አልዋጥ ያላቸው የአሃዳዊ ስረአት ውረዴዎች ናቸው። እርግጥ በብሄር፣ ብሄረሰቦች መብትና ነፃነት ዙሪያ ግንዛቤ የሌላቸውና የብሄሮች፣ በሄረሰቦች ቀንን የማክበር ዓላማ ያልተረዱ ሊኖሩ እንደሚችሉ ይገመታል።

ያም ሆነ ይህ ኢትዮጵያ ብሄሮቸ፣ ብሄረሰቦችና ህዘቦች ቀን ተከበሯል። ለወደፊትም መከበሩ የቀጥላል። እለቱ የኢፌዴሪ ሀገመንግስት በፀደቀበተ  ህዳር 29 ላይ ነው የሚከበረው። የኢፌዴሪ ህገመንግስት ከሃያ ዓመት በፊት ህዳር 29፣ 1987 ዓ/ም ነበር የፀደቀው። የኢፌዴሪ ሀገመንግስት በፊወዳላዊው የዘውድ ስርአት ግዛት የማስፋት ወረራ አሃዳዊ ኢትዮጰያ በሃይል ከተመሰረተችበት የ19ኛው ክፍለ ዘመን ማገባደጃ ጀምሮ በኢትዮጵያ በሄሮች፣ ብሄረሰቦቸና ሕዝቦች ላይ የተጫኘነው ብሄራዊ ጭቆና እና ለዘለቄታው ማንነታቸውን የማጥፋት ስትራቴጂ ተግባራዊነት እነዲያበቃ ያደረገ ህገመንግስት ነው።

ዘውዳዊው ስርአትና ይህንኑ ስርአት ሲያገለገሉ በነበሩ ጥቂት ወታደራዊ መኮንኖች አምባገነናዊ ስርአትም ያነኑ የዘወዳዊ ስረአቱ ሲከተለው የነበረውን በሄራዊ ማንነቶችን በማጥፋት አሃዳዊ ስርአት የመመስረት ስትራቴጂ ከማሰቀጠለ ያለፈ አዲሰ ነገረ አላመጣም። በመሆኑም በዚህ ስረአት ተጠናክሮ የቀጠለወ በሄራዊና ኢኮኖሚያዊ ጨቆና ስረአቱን የሚታገሉ የብሄረዊ ነፃነት ግንባሮች እነዲፈጠሩ አደረገ። ከጭቆና ለመላቀቅ የተመሰረቱት ብሄራዊ የነፃነት ግንባሮች ከፍተኛ የህይወት መስዋዕትነት የጠየቀ እልህ አስጨራሽ የትጥቅ ትግል አካሂደዋል።

እጅግ ከፍተኛ ቁጥር ያለውን የሃገሪቱን ሕዝብ የሚወክሉ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ላይ የተጫነው አስከፊ በሄራዊ ጭቆናና ከዚህ ጭቆና ለመላቀቀ የተከፈተው የትጥቅ ትግል የብሄሮችና ብሄረሰቦች የመብት ጥያቄ የኢትዮጵያ ፖለቲካ መሰረት እንዲሆነ አድርጓል። ለዚህ የመብትና ነፃነት ጥያቄ ምላሽ ሳይሰጥ ሃገሪቱን በነበረችበት ማስቀጠል የማይታሰብ ነበር።

በ1983 ዓ/ም ግንቦት ወር ላይ የመጨረሻው አሃዳዊ አምባገነን የመንግስት ስርአት - ወታደራዊው ደርግ የተገረሰሰውም እነዚህ ብሄራዊ ነፃነት ግንባሮች በየአቅጣጫው ባካሄዱት የትጥቅ ትግል ነበር። አምባገነን የመንግስት ሥረኣት ሲመራ የነበረው ወታደራዊው ደርግ በተገረሰሰ ማግስት፣ በሃገሪቱ ከዚያ ቀደም የነበረውን በህዝቦች መሃከል የነበረ ጭቆናና ጭቆናው ያስከተለውን የተዛባ ግንኙነት የሚሽር አዲስ የመንግሥት ሥርአት መገንባት አስፈላጊ ሆነ። በመሆኑም የደርግን መንግስት በትጥቅና በተለያየ መንገድ ሲታገሉ የነበሩ በሃገር ውስጥና በውጭ ሃገራት የነበሩ ሁሉም ተቃዋሚ ኃይሎች የኢትዮጵያን መፃኢ እጣ ፈንታ ለመወሰን በአንድ አዳራሽ ተሰበሰቡ። ያለማንም ገፊነትና ታዛቢነት በራሳቸው ተነሳሽነት ነበር ይህን ያደረጉት።

የኢትዮጵያን መፃኢ ዕጣ ፈንታ ለመወሰን ከታደሙት መሃከል ሃያ ገደማ የሚሆኑት አሃዳዊ አምባገነን ስርአቱን ለማስወገድ የትጥቅ ትግል ያካሄዱት የብሄራዊ ነፃነት ግንባሮች ነበሩ። እነዚህ የነፃነት ግንባሮች ባካሄዱት መራራ ትግል የወታደራዊውን ደርግ መንግስት ከስሩ ነቅለው እንዳስወገዱ ለአጭር ግዜ መላ ሃገሪቱን የሚያስተዳድር መንግስት አልነበረም። እርግጥ ደርግን በመደምሰስ ትግል ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ የነበረውና ከፍተኛ ቁጥር ያለውን የኢትዮጵያ ህዝብ የሚሸፍኑትን የኦሮሞ፣ የአማራና የትግራይ ብሄሮች የነፃነት ግንባሮች አቅፎ የነበረው ኢህአዴግ ለአንድ ወር ያህል ሰላምና መረጋጋትን የማስፈን ሃላፊነትን ወስዶ ነበር። ይህም ቢሆን ግን የየብሄሩ የነፃነት ግንባሮች በየአካባቢያቸው የየራሳቸውን መንግስት መስርተው በቀጥታ የመገንጠል ጥያቄ ማንሳት የሚችል የመበታተን አደጋ በተጨባጭ ነበር። ሃገሪቱ ልትበታተን የምትችልበት ጠርዝ ላይ ደርሳ ነበር ማለተ ነው።

ታዲያ የትጥቅ ትግል ያካሄዱት ብሄራዊ የነፃነት ግንባሮች የየራሳቸውን ነፃ መንግስት የመመስረት ዕድል በእጃቸው የነበረ ቢሆንም፣ ይህን ከማድረግ ይልቅ አብረው መኖር የሚችሉበትን ሁኔታ ይኖር እነደሆነ ወደመፈለገ ነበር ያመሩት። አብረው መኖር የሚችሉበት አማራጭ ይኖር እነደሆነ እንዲፈልጉ ያነሳሳቸው ተገንጥሎ ነፃ መንግስት መመስረት በራሱ ብሄራዊ ጭቆና ወደሌለበት ሥርአት የሚወስድ ብቸኛው አማራጭ ሳይሆን፣ የመጨረሻው አማራጭ መሆኑን መገንዘባቸወ ነበር።

እናም ከዚህ በመነሳት የኢትዮጵያ የተቃውሞ ፖለቲካና የነፃነት ትግል መሰረት የሆነው ብሄራዊ ጭቆና የሌለበትንና በእኩልነት መኖር የሚችሉበትን ሥርአት ለመመስረት ተስማሙ። በዚህ መሰረት የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች ተሰባስበው የደርግን ሥርአት ለመጣል ባበረከቱት አስተዋፅኦና በሚወከሉት ሕዝብ ቁጥር ልክ ሥልጣን የተጋሩበት የሽግግር መንግስት መሰረቱ።

የዚህ የሽግግር መንግስት ቀዳሚ ዓላማ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች በመቻቻልና በመከባበር ላይ በተመሰረተ አንድነት  የሚኖሩበትን የመንግስት ሥርአት መመሥረት ነበር። ይህ መንግስት የሚመራበትን ህገመንግስት መቅረፅ የዚህ የሽግግር መንግሥት ዋና ተልዕኮ ነበር።

በዚህ መሰረት ሁሉም የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች እንዲሁም በሌሎች አመለካከቶች የተደራጁ ፓርቲዎች የተወከሉበት የህገመንግስት አርቃቂ ኮምሽን ተቋቋመ። ይህ ኮምሽን የመጀመሪያውን የህገመንግሥት ረቂቅ አዘጋጀ። ረቂቁን ኮምሽኑ ራሱ ወይም ከፍተኛው የስልጣን አካል የሆነው የሽግግር መንግሥቱ ምክር ቤት እንዲያፀድቀው አልተደረገም። ከዚህ ይልቅ የህገመንግስቱ ባለቤት የሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲያፀድቀው ነበር የተደረገው።

በቅድሚያ በኢትዮጵያ ብሄሮችና ብሄረሰቦች የሚወከሉ ሁሉም ለአካለ መጠን የበቁ ኢትዮጵያውያን በረቂቅ ህገመንግስቱ ላይ አንቀፅ በአንቀፅ እንዲወያዩ ተደረገ። በዚህ ውይይት፣ መቀነስ አለበት ያሉትን ቀንሰው፣ መጨመር አለበት ያሉትን አክለው ረቂቁን በማዳበር መልሰው ላኩት። ኮምሽኑ በህዝብ ዳብሮ የተላከለትን ረቂቅ አሻሽሎ ሕዝብ

ለሁለተኛ ግዜ እንዲወያየበት ወደ ሕዝብ መራው። ረቂቁ ለሁለተኛ ግዜ የተመራለት የኢትዮጵያ ህዝብ ልክ እንደመጀመሪያው አንቀፅ በአንቀፅ አድቅቆ ተወያይቶ ማሻሻያ ሃሳቦችን አካቶ ላከው።

ከዚህ በኋላ ይህ ሁለት ግዜ በህዝብ ውይይት የዳበረ ረቂቅ ሕገመንግሥት ወደመፅደቅ ሂደት ተሸጋገረ። የፀደቀው በአርቃቂ ኮምሽኑ ወይም በሽግግር መንግሥቱ ምክር ቤት አልነበረም። በሕዝብ ነበር የፀደቀው። ህዝብ በመረጣቸው ተወካዮች።

ሁሉም በሕገመንግስቱ ላይ የተወያዩ የተለያዩ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች አባላት የሆኑ ለአካለ መጠን የደረሱ ኢትዮጵያውያን በምስጢራዊ የድምፅ አሰጣጥ ሥርአት የህገመንግስት አፅዳቂ ጉባኤ አባላትን መረጡ። ምርጫው የተለያየ አመለካከት ያላቸው ወገኖች የተሳተፉበት፣ ነፃና ዴሞክራሲያዊ ነበር። በዚህ ነፃና ዴሞክራሲያዊ በሆነ ምርጫ የተመረጡ አባላትን የያዘው የህግመንግስት አፅዳቂ ምክር ቤት ሁለት ግዜ በሕዝብ ውይይት የዳበረውን ረቂቅ ሕገመንግስት እያንዳንዷን አንቀፅ በድምፅ ብልጫ እያሳለፈ በመጨረሻ ሙሉውን ህገመንግስት አፀደቀ።

የዚህ ህገመንግስት ባለቤቶች፣ ራሳቸውን በራሳቸው እያስተዳደሩ እርስ በእርስ በመከባበርና በመቻቻል በእኩልነት የሚኖሩበትን የመንግስት ሥርአት መመስረት የቻሉ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዘቦች ናቸው። የኢፌዴሪ ሕገመንግሥት የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው እያስተዳደሩ በእኩልነት ለመኖር የተስማሙበት የቃልኪዳን ሰነድ ነው።

የኢፌዴሪ ሕገመንግስት ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዘቦቸ የኢትዮጵያ ሉአላዊ ስልጣን ባለቤቶቸ መሆናቸውን ይደነግጋል። በህገመንግስቱ አንቀፅ 8 "የህዝብ ሉዓላዊነት" በሚል ርዕስ ስር በንኡስ አንቀፅ 1 ላይ *"የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦች፣ ሕዝቦች የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ስልጣን ባለቤቶች ናቸው።"* ተብሎ ተደንገጓል።

ሕገመንግስቱ ለኢትዮጵያ ብሄሮች፣ በሄረሰቦችና ሕዘቦች ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር እስከመገነጠለ የዘለቀ መብት ይሰጣል። በአንቀፅ 39 "የብሄሮች፣ በሄረሰቦችና ሕዘቦቸ መብት" በሚል ርእስ ስር፤

- *ማንኛውም የኢትዮጲያ ብሄር፣ ብሄረሰብ፣ ሕዝብ የራሱን እድል በራሱ የመወሰን እስከመገንጠል ያለው መበቱ በማናቸውም መልኩ ያለገደበ የተጠበቀ ነው።*
- *ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሄር፣ ብሄረሰብ፣ ሕዝብ በቋንቋው የመናገር፣ የመፃፍ፣ ቋንቋውን የማሳደግ እና ባህሉን የመግለፅ፣ የማዳበርና የማስፋፋት እንዲሁም ታሪኩን የመነከባከብ መብት አለው።*

በሚል ተደንግጓል።

እነዚህ ከላይ የተገለፁ ሁኔታዎች የብሄሮች፣ በሀረሰቦችና ሕዝቦች መብትና ነፃነት የኢፌዴሪ ሕገመንግስት መሰሶ መሆኑን ያመለክታሉ። የኢፌዴሪ ህገመንግስት ማንነታቸው እውቅና ተነፈጎት የነበረውን የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ በሄረሰቦችና ህዝቦች ማንነታቸው በህግ እውቅና እንዲያገኙና ራሳቸውነ በራሳቸው የማሰተዳደረ መብትና ነፃነት ባለቤቶቸ እንዲሆኑ አድርጓል። እንዲሁም አንዱ ትልቅ ሌሎች ትንሽ፣ አንዱ ዋና ዜጋ ሌሎቸ አናሳ ዜጋ፣ አንዱ ታማኝ ሌሎች ለሃገራቸው የማይታመኑ . . . ተደረገው በመሃከላቸው ተፈጥሮ የነበረውን የተዛባ ግንኙነት በማስተካከል በመፈቃቀድ፣ በመከባበርና በእኩለነት ላይ የተመሰረተ ጠንካራ የህዝቦች አንድነት ያላት ሃገር መመሰረት አስቸሏል። የብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች መብትና ነፃነት መረጋገጡ በሃገሪቱ ሰላም እንዲሰፍን አድርጓል። ይህ ሰላም ደግሞ ለእድገትና ልማት አመቺ ሁኔታን ፈጠሯል። ባለፉ አስራ ሁለት ዓመታት የተመዘገበው ዓለም የመሰከረለተ በሕዝቡ ኑሮ መሻሻል የተገለፀ እድገት ህገመንግስቱ ባረጋገጠው ሰላም ዕውን መሆን የቻለ ነው።

የወሰን ሳይሆን የህዝቦች አንድነት ያላት ጠንካራ ኢትዮጵያ እንድትፈጠር፣ ሰላም እንዲሰፍንና የህዝቡን ኑሮ ወደተሻለ ደረጃ የሚያሸጋግር እድገት እንዲመዘገብ ማድረግ ያስቻለ የኢፌዴሪ ሕገመንግስት በሃገሪቱ ታሪክ ውስጥ ከምንም በላይ የላቀ ትልቅ ዋጋ አለው። በመሆኑም ይህ ህገመንግስት የፀደቀበትንና ለብሄሮች ብሄረሰቦችና ሕዝቦች እውቅና

ሰጥታ መብታቸውን ወዳረጋገጠች አዲሲቱ ኢትዮጵያ የተሸጋገርንበትን ታሪካዊ አለት መዘከርና ማክበር አሰፈላጊ ነው። ይህ እለት ሕዳር 29 ነው።

ዕለቱ የሕገመንግስቱ ዋነኛ መሰሶ የሆኑትና ማነነታቸው ተከበሮ የሉዓላዊ ስልጣን ባለቤትነታቸው ተረጋግጦ በአንድነት ለመኖር በሀገመንግስቱ ቃል ኪዳን በገቡት በሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀንነት እንዲዘከረ ተደርጓል። ይህም አስፈላጊ ነው። የኢተዮጵያ ሉዓላዊ ስልጣን ባለቤቶች ብሄሮቸ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች በመሆናቸው፣ "ገመንግስቱም የቃል ኪዳነ ሰነዳቸው በመሆኑ እንዲሁም ያለበሄሮቿ፣ ብሄረሰቦቿና ሕዝቦቿ የአሁኗ ኢትዮጵያ ልትኖር ስለማትችል።

ታዲያ የኢትዮጵያ በሄሮች፣ በሄረሰቦችና ሕዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው እያስተዳደሩ በመከባበረ ላይ የተመሰረተ አንድነት ኖሯቸው ለመኖር ቃለ የገቡበት ሀገመንግስት የፀደቀበትን የብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ቀን፣ በአንድ ስፍራ ታደመው የማንነታቸው መገለጫ የሆኑ ትእይንቶችን በማቀረብ በልዩነት ውስጥ ያለውን አንድነታቸውን በሚያሳይ ሁኔታ ያከብራሉ። የአንድ ብሄር፣ በሄረሰብ ወይም ሕዝብ የማንነት መገለጫ ከሆኑ ነገሮች ውስጥ አንዱ ባህል ነው። አልባሳት፣ ጭፈራና ዜማ ደግሞ የባህል እሴቶች ናቸው። የብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀን ሲከበር በአከባበር ስርአቱ ላይ አለባበስ፣ ጭፈራና ዜማ የመሳሰሉ የማንነት መገለጫዎች መታየታቸው በራሱ መድረሻ አይደለም። መድረሻው ማንነታቸው የተከበረበትና እኩልነታቸው ተረጋገጦ በለዩነት ውስጥ ባለ አንድነት ላይ የተመሰረተችው ኢትዮጳያ ሉዓላዊ የስልጣን ባለቤቶች መሆን ያስቻላቸውን ሕገመንግስትና ሕገመንግስታዊ ስረአት መዘከር ነው።

የኢትዮጵያ የብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ቀን መከበር ሁሉም የማንነት መገለጫዎቻቸውን በማውጣት በአንድ ቦታ ላይ በመታደም አንዱ ሌላውን እንዲያውቅ፣ በመሃከላቸው ያለውን መከባበርና መቻቻል እነዲገለፁ ማደረግ የሚያስችል ሁነት የፈጥራል። ይህ ሁነት በልዩነት ውስጥ ያለውን አንድነታቸውን ሊታይ በሚችል ደረጃ ተጨባጭ አድርጎ ያቀርበዋል።

የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች በአል አከባበር ጥቂቶች እንደሚሉት ባዶ የጭፈራ ሁነት ሳይሆን የህዝቦች አንድነት የሚጠናከርበት፣ በዚህም ዘላቂ ሰላምና ልማት የሚረጋገጥበት ታላቅ ታሪካዊ መሰረት ያለው ሁነት ነው። እናም በአሉን በተመለከተ “የብሄሮች ብሄረሰቦች ምብት እከመጨፈር” በሚል የተሰነዘረው ቧልት ሞቶ የተቀበረው አሃዳዊ  ስርአት አመለካከት ውርዴዎች የተናገሩት የዘቀጠ ስብእና ውጤት ነው።

**ይቀጥላል**